# «እነሱ» ማለት «ለነሱም» ይሆናል!!

በሃገራችን ያለውን የምርጫ ሁኔታ በሰለጠነው ዓለም ከሚታየው የሠለጠነ ፖለቲካ አካሄድ ጋር 100 በ100 እናስተካክለው ብንልም የሚሆን ቀርቶ የሚሞከርም አለመሆኑ በተደጋጋሚ መግለጫም መመርያም ማስፈራሪያም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ እሩቅ መሄድ ዋቢ መጥቀስ ምስክሮች ከየጉራንጉሩ ሰብስቦ ሥልጠና ሰጥቶ ለድካማቸውና ለክህደታቸው ሂሳብ ከፍሎ ማዘጋጀትም አያስፈልግም፡፡

ዝም ብሎ የምርጫ 97ን ሁኔታ ማጤኑ ብቻ በቂ ይሆናል፡፡

ቅድመ ምርጫ ጠ/ሚኒስትሩ ለሃገርም ውስጥ ለውጭም ሰዎች (እርግጥ አሁን እሳቸውም ሰዎቻቸውም ከውጭዎቹ ጋር ብዙም ፍቅር የላቸውም) «ይህ ምርጫ እንከን የለሽ ምርጫ ነው የሚሆነው» በማለት በተደጋጋሚ መግለጫ ሰጥተውበት እንደነበር የነምናስታውሰውና ልንረሳውም የማንችለው ጉዳይ ነው፡፡ «እንከን የለሽ» የሚለው አባባል ለወቅቱ እንደፋሽን ተይዞ ጠ/ሚኒስትሩ በተነፈሱት ማግሥት አቶ በረከት ስምኦን ተቀብለው እንዳይረሱት ይመስላል ጠዋት ቀን ማታ «እንከን የለሽ» ካላሉ ይታመሙ ይመስል ፀሎታቸው አርገውት ነበር፡

አንዳንድ ሰዎች አባባሉ እጅ እጅ ብሏቸውና ወደ ተግባር የመለወጡ አካሄድ ከቃሉ ጋር እየተጣረሰ ሲያዩት « ምናለ እኚህ ሰው ቃሉን ወደውት ከሆነ ውሻ አሳድገው ስሙን እንከን የለሽ ቢሉት» እስከ ማለት ደርሰው ነበር ይባላል፡፡

«ገዢው ፓርቲ ፓርቲም መንግሥትም ሆኖ ነው ችግራችን፤እንደፓርቲ ይወዳደራል እንደመንግሥት ለራሱ የሚጥመውን እየመረጠ ሕግ ያደርጋል፤ተቃዋሚዎችን በፍራቻ ጠልቶ ሕዝቡን ካልጠላህ ወየውልህ በማለት ያስፈራራል፡፡

እንደፓርቲ ሲወዳደር ለዚሁ ውድድሩ መንግሥት ይሆንና ሰዉን፤ንብረቱን ቁሳቁሱን ተሽከርካሪውን ገንዘቡን ያዝበታል፡፡

እንደፓርቲ ስብሰባ ይጠራል ይሰበስባል የፈለገውን ይላል እንደመንግሥት ተቃዋሚዎች ስብሰባ እንዳይጠሩ ያዛል መመርያ ለፈቃጁ ክፍል ይሰጣል ሕዝቡን ከፀረ ሕዝቦች ጋር አትሰብሰቡ ይላል ስም ያጠፋል፡፡

እንደፓርቲ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ሃሳቡን ይገልፃል ለሕዝብ የምረጡኝ ተማጽኖ ያሰማል ወዲያው እንደመንግሥት ደግሞ ተቃዋሚዎች በመገናኛ ብዙሃን ሊጠቀሙ የሚችሉበትን የተጣበበ ህግ ያወጣል መገናኛ ብዙሃኑን ያዛል ይመራል ይከለክላል፡፡የተቃዋሚዎች መግለጫም ሆነ ሕዝባዊ ጥሪ መልዕክት እንዳይተላለፍ ይወስናል ያግዳል፡፡በመገኛኛ ብዙሃኑ እንደፓርቲም መንግሥትም ተቃዋሚዎች የሰይጣን ቁራጭ ናቸው ብሎ እራሱን ይገልጸበታል፡፡

እንደፓርቲ በምርጫ ቦርድ ይመዘገባል፤እንደመንግሥት ምርጫ ቦርድ ውስጥ የሚሰሩትን ሰዎች ይመድባል፤የምርጫ ቦርድን መተዳደርያ ደንብ ያወጣል፤የተቃዋሚ ድርጅቶችን በተመለከተ አሳሪ ደንብ አውጥቶ አጽድቆ መመርያ በማድረግ እንቅስቃሴያቸውን ያግዳል፡፡የምርጫ ጣቢያዎችን ያቋቁማል ሰዎች ይመድባል ታጣቂ ሃይሎች ያሰማራል ተቃዋሚዎች ምርጫውን በፍርሃት እንዲሸሹት ያደርጋል አሻፈረኝ መብቴ ነው ያሉትን ደሞ ምዝገባ ያስከለክላል ከዚያም አልፎ ያስራል፤

እንደ ፓርቲ የምርጫ ሂደትን በተመለከተ ይከሳል ተጭበረበርኩ ይላል እንደመንግሥት የተቃዋሚ አሸናፊዎችን ያስራል፤ምርጫውን ይክዳል ኮረጆውን ያስነጥቃል ተሸናፊ አባሎቹ አሸናፊ እንዲባሉ ለሚመለከታቸው ሁሉ መመርያ ያስተላልፋል፡፡

እንደፓርቲ የውጪ ታዛቢዎች እንዲገቡና እንዲመለከቱ ይስማማል ወግነውት ካልቆሙና እሱን ደግፈው ውጤቱም እሱን በሚጠቅመው መልኩ እንዲሆን ካላደረጉ በስተቀር እንደ መንግሥት ወደመጡበት እንዲመለሱ ያደርጋል የሰጡት መግለጫም

በሃገር ሉአላዊነት ላይ የሚደረግ ደባ ተብሎ ታርጋ ይወጣለትና ትላንት አክብሮ የተቀበላቸውን በስድብ ናዳ ያባርራል፡፡

በምርጫ 97 ይህና ከዚህም የባሰ ነው የተከናወነው፡፡
ሕይወት ጠፍቷል
ንብረት ጉዳት ደርሶበታል
ንጹሃን ዜጎች ሃሳባቸውን በነጻ ስለገለጹ ታስረዋል ተደብድበዋል
መብታቸው ነው ተብሎ በሕገ መንግሥቱ ላይ የሰፈረው ተጥሶ በምርጫ ያመኑበትን ስለመረጡ ከሥራ ተባረዋል ለስቃይ ተዳርገዋል መከራ ፍዳ ቆጥረዋል
አሸናፊነታቸውን በምርጫ ካርድ ያረጋገጡ ፓርቲዎች ማን አሸንፉ አላችሁ አይነት በምርጫ ማሸነፍ ወንጀል ሆኖባቸው ታስረዋል
ሕዝቡ ይበጀኛል ላለው ፓርቲ ድምጹን በመስጠቱ እስካሁንም መከራውን እያየ ነው፡፡

## በምርጫ 97 ሃገርና ሕዝብ ችግር ደርሶባቸዋል

ያን ጊዜም ልክ እንደዛሬው ወጣቱ ተሰብስቦ የምርጫ መመርያ በጠ/ሚኒስትሩ ተሰጥቶት ካናቴራም ታድሎት ነበር ለምርጫ የተሰማራው፡፡ያንጊዜም መመርያውንም ሰምቶ ካናቴራውንም ተቀብሎ ወደ ምርጫው ሲሄድና ካርዱን ሲሰጥ ግን በመመርያው ተመርቶ ሳይሆን በሕሊናው ተማምኖ ነበር፡፡ለንናቴራው ብሎ ሳይሆን ለዘላቂው ሕይወቱ አስቦና ወስኖ ነበር፡፡

ዘንድሮም እንዳምናው ጠ/ሚኒስትሩ ወጣቱን ሰብስበው መመርያ ሰጡት፡፡ ካች አምና የነበረው ወጣት ዘንድሮም ነበር ልዩነቱ የበለጠ ምሬት አለበት፤የበለጥ የኑሮው ውድነት አሳሩን እያሳየው ነው፤ዘንድሮ በሄደበት ሁሉ የአባልነት ፎርም ካልሞላህ አትተነፍስም አትራመድም አትቆምም አትቀመጥም እየተባለ ግራ ተጋብቶ መከራ ላይ ነው፡፡

ዘንድሮም የካች አምናው ወጣት «እነሱን» አትስማቸው ሊያታልሉህ ሊዋሹህ አሁንም ተዘጋጅተዋል በማለት እንዳይመርጥ አያከላከሉት ነው፡፡እርግጥ ስም አልጠሩም እነሱ ነው ያሉትና «እነሱ»የሚለው አባባል «ለነሱም» ሊሆን ይችላል ነበር ያለው ወጣቱ ከስብሰባው አዳርሽ ሲወጣ፡፡

ጠ/ሚኒስትሩ ይህን ስብሰባ የጠሩት እንደሕወሃት ሊቀ መንበርነታቸው ነው?
እንደኢህአዴግ ሰብሳቢነታቸው ነው?
እንደጠቅላይ ሚኒስትርነታቸው ነው?
እንደጦር ኃይል አዛዥነታቸው ነው?
እንደምክር ቤት አባልነታቸው?

ጠ/ሚኒስትሩ ይህን ስብሰባ ሲያቅዱ ዝም ብለው የሚመለከታቸውን ጠርተው «ወጣቱን ስብሰባ ቦታ አዘጋጅታችሁ ጥሩልኝ» አሉ

ወይስ ለአዲስ አበባ መስተዳደር ደብዳቤ ተልኮ አስፈላጊውን ፎረማሊቲ አሟልተው ተፈቀደላቸው?

ምናልባት ጠ/ሚኒስትሩ ስብሰባ አድርገው እንዲያነጋገሩዋቸው ወጣቶች ይሆኑ የጠየቁት?

ለመሆኑ በዚህች በፈረደባት በኛ ሃገር ላይ
ለሕወሃት አንድ
ለኢህአዴግ ሌላ አንድ
ለሕወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ ደሞ ሌላ
አንድ ለኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ

ደሞ አሁንም ሌላ አንድ ለጠ/ሚኒስትሩ ደሞ ሌላ አንድ ሕገ መንግሥቶች አሉ ወይስ ሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች በአንድ ሕገመንግሥት ነው የሚተዳደሩት?

በተለያየ ሕገመንግስት ከሆነ አያጠያይቅም፡፡በአንድ ነው ከተባለ ግን ያ የሚያጠያይቅ መሆኑ ከታመነበት ውሎ አድሯል፡፡ታዲያ ካለፈው ስህተት በመነሳት

ይስተካከላል ተብሎ የታሰበው ጭራሹን ደብዛው እየጠፋ ሲሄድ እያየነው ነው፡፡ይህንኑ መሰረት ባደረገም ይመስላል ጠ/ሚኒስትሩ «እነሱ» ሲሉን የዋሉት፡፡እነሱ የሚለው ወጣቶቹ እንደቀለዱት «ለነሱም» የሚሆን ነው፡፡

ክቡር ጠ/ሚኒስትር

ካች አምናም እኮ ዘንግተውት ካልሆነ በስተቀር እንደዚሁ እንደ ዘንድሮው «እንከን የሌለበት» ብለውን ነው በኋላ ሁሉም ነገር «እንከን በእንከን» የሆነው፡፡እንደዕውነቱ ከሆነ ካች አምና በጥቂቱም ቢሆን ይሻል ነበር ምነው ቢሉ «እንከኑ»የጀመረው ትንሽ ዘግይቶ፤ አካሄዱ ኢህአዴግ እንዳሰበው አልሆን ማለት ሲጀምር ነበር፡፡ ያሁኑ ግን ፈጠነ፡፡ከነፋስም ቀደመ፡፡ገና ምኑም ሳይያዝ በአንድ ስብሰባ ያውም በመብራት ሀይል ግቢውስጥ በጠባቡ በተካሄደ ስብሰባ በመደናገጥ እስር መጀመሩ የካች አምናው እንዲያው በጥቂቱ ይሻል ነበር! ያሰኛልና እባክዎ ያንን «እንከን የለሽ» የሚል ነጠላ ዜማ ገዢ ያጣ ሆኗልና መልሰው ለገበያ አያቅርቡት፡፡

አንዳንድ ስህተቶች ድንገት ካለማሰብ ወይም በችኩሎች አለያም በማን አለብኝነት ይፈጸሙና ማጣፊያው ጠፍቶ ግራ ማጋባት፤ውሉን ፍለጋ መዳከርን ያስከትላሉ፡፡ባለፈው ምርጫ ማግስት የታየውና ለገዢው ፓርቲ ፈታኝ መከራ ያስከተለበትም ይሄው አካሄድ ነበር፡፡ከዚያ መማር ሳይቻል ቀርቶ አሁንም ያው አይነት አካሄድ እየተደገመ መውጫው እየጠፋ የባሰውን ነገር እያበላሸ እያቆራረጠ ነው ያለው፡፡ ለአንድ ጊዜ ረጋ ብሎ ማሰብ ከችግር ያድናልና ርጋታ ያስፈልጋል፡፡

ጠ/ሚኒስትር

ወጣቱ እኮ የጋሪ ፈረስ አይደለም፡፡ወጣቱ እኮ የርስዎንም ፓርቲ ሌሎቹንም እርስዎ ተቃዋሚ የሚሏቸውን ወጣቱ ግን አማራጭ ወይም ተፎካካሪ የሚላቸውን አሳምሮ ያውቃቸዋል፡፡ከነዚህም መሃል የቱ ዕውነትንና ሕዝባዊነትን የቱ ደሞ ለሥልጣንና ለጥቅም የቆመ?የቱ ተገዝቶ እንዳለ በሚገባ ተረድቶ ያገናዘበ ነው፡፡

ወጣቱ እኮ እየተጠራ ሲመጣ ወዶ እንዳይመስልዎት አብዛኛው በሚኖርበት ጥቂቱ የታደለው ደሞ በሚሰራበት ከተሰጠው ማስጠንቀቂያ ሃይል የተነሳ የተገኘ ነው፡፡ያ ባይኖር እንኩዋንስ የሚሌ ነማ (በኦሮምኛ የሰው እግር ማለት ነው) አዳራሽ ቀርቶ የቀበሌ አዳራሽ የሚሞላም ተሳታፊ መገኘቱን እንጠራጠራለን፡፡

ወጣቱ በራሱ ሕሊና የሚመራ ሁሉንም ባለፉት 18 ዓመታት አይቶ መዝኖ ያወቀ ነውና ማስፈራራቱ ማዋከቡ በጥቅማ ጥቅም ለመደለል መረብ መዘርጋቱ ይቅርና ነጻ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ የሆነ ምርጫ እንዲካሄድ መንገዱ ይመቻች፡፡እስቲ ለታምር እንዲሆን፤ዓለምም እንዲደነግጥ ምናለበት ከምር ንጹህ ምርጫ ለማካሄድ የሚቻልበትን መንገድ ቢያስተካክሉ? ሕዝብም ታሪክም እስከዛሬ ለተፈጸመው ግፍና በደል ሁል ይቅር እንደሚል አይጠራጠሩ፡፡

ጠ/ሚኒስትር አንድ ብርቱ-ካህንን በማሰር የሕዝቡን ፍላጎት ማሰር አይቻልም፡፡በማስፈራራት ሰውን ከፍላጎቱ ማራቅም አይታሰብምና ደጋፊዎችዎንና አባሎችዎን ወደ ሕሊናቸው እንዲመለሱ ይምከሩ ይዘዙ በርቱ ይበሉ፡፡ወቅቱ አሁን ነው፡፡

አንዲት ወጣት፤ጎበዝ፤ቆርጥ፤እንስት፤ መሪነቷን ሕዝብ የተቀበላትን አስረው እኛ ን ልፍስፍስ መሰለን የታየንዎትን ስብሰባ መጥራትዎ በወጣት ብርቱ-ካህን ላይ እንድንዶልት ነው?ብርቱ-ካህንን እንድንጠላ ነው? ከብርቱ-ካህን እንድንርቅ ነው?

ይሄ ጨርሶ የማይታሰብ ነው!!፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር!

ለመሆኑ ባጠግብዎ ያሉት የሴት አመራር አባላት የሚባሉት እስካሁን ምን የፈጸሙት ሃገራዊ ወይም ድርጅታዊ ተግባር አለ?

ሊኖር አይችልም ምክንያቱም እነሱ ያላቸው ሆዳዊ ተግባር ነውና፡፡ለመሆኑ የያንዳንዳቸውን ባሕሪ ለይተው ያውቁታል፡፡

ብቻ ባሕሪ ሳይሆን አመል ያላቸው በመሆናቸው ሊያውቁትም አይችሉም እንጂ ቢኖራቸውና ቢያውቁት ምን ያህል ውርደት እንደሆነ ይገነዘቡት ነበር፡፡

ስንት አየን ዘንድሮ ከአማናውም የባሰ<br>
ጎርሶ አደር አሉን ከገንዳ እየላሰ

ውሸት ተለመደ ሐሰትም ነገሰ
ገበሬ ሞፈሩን ሰቅሎ፤ እየፈለሰ
ጠግቦ አደረ አሉን እሱ መች ቀመሰ?
ሎተሪ አዟሪ
ሴተኛ አዳሪ የአዲስ አባን አስፓልት
ጎርሶ አደረ አሉን በአፈጠጠ ውሸት
ምእራፊ ጥብቆ
አንጀቱ ተጣብቆ
የሰው ልጅ ሲማጸን
እመንገድ ዳር ወድቆ
ምነው አልታያቸው የሱ ጣር ለነሱ
በስሙ  እርዳታ እያግበሰበሱ
ጠብታ እንኳዋን ላፉ ከንፈር ሳያርሱ
ሽቅርቅር መኪና እያንፈላሰሱ
ትንሽም አያፍሩ ለምርጫ ሲነሱ?
አይቸኩልም እንጂ ፍርዱ የፈጣሪ
አንድ ቀን ይደርሳል ልክ እንደሎተሪ
የዚህን ሁሉ እንባ ግፍ ቆጥሮ በቀኑ
ወይ መጽደቅ አይቀርም ወይም መኮነኑ!!
ዳግም እንከን የለሽ አይሠራም በቅቶታል
እርስዎም አይልፉ ነገሩ ገብቶናል፡፡

ብሎ የገጠመው ወጣት ባለፈው 97 ምርጫ አንድ የቤተሰብ አባል በአግአዚ ጥይት፤በእርስዎ ትዕዛዝ፤በበረከት አዝማችነት ያጣ ወጣት ነው፡፡ አዩ ያ ቤተሰብ ያጣም ወጣት የቤተሰቡ ገዳይ በጠራው ስብሰባ ላይ መምጣቱ ወዶ ይመስልዎታል?ፈርቶ ነው ብለው ያምናሉ?እንደዚያ አስበው ከሆነ ተሳስተዋል፡፡ወደ ስብሰባው የመጣው ከካች አመንው የተለየ ነገር ቢኖር ለመስማት ነበር፡፡የሰማው ግን የተለየ ሳይሆን ያንኑ ያምናውን ዜማ ነበር፡፡

ስለዚህም አዲስ ዜማ ይሄውልዎት፡፡
ርዕሱን ለጊዜው፡፡

«እኛም አውቀናል ጉድጓድ ምሰናል»
ባተሌው ወጣት ነኝ